አጠቃላይ መመሪያ

መመሪያዎቹን በጥንቃቄ አንብቡ። ስለፈተናው ጥያቄዎች ካላችሁ ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ፈታኙን /ፈታኟን / መጠየቅ ትችላላችሁ። ፈተናው ከተጀመረ በኃላ ምንም አይነት ጥያቄዎች መጠየቅ አይቻልም ።

ለዚህ ፈተና የተሰጠው ጊዜ 1 ሰዓት ብቻ ሲሆን ከተሰጠው ሰዓት በላይ መስራት አይፈቀድም ከተፈቀደው ጊዜ ቀድማችሁ ከጨረሳችሁ የሠራችሁትን ፈተና መከለስ ትችላላችሁ ።

እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አማራጮች ያሉት ሲሆን ጥያቄዎቹንና ምርጫዎቹን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኂላ መልሳችሁን በሚስጣችሁ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በትክክል አጥቁሩ። መልሳችሁን ለመቀየር ከፈለጋችሁ የመጀመሪያውን መልስ በደንብ አጥፍታችሁ የተቀየረውን መልስ አጥቁሩ::

ፈተናውን ለብቻችሁ መስራት ይኖርባችኂል። በማንኛውም መንገድ ለማጭበርበር ከሞከራችሁ ውጤታችሁ በሙሉ ይሠረዛል።

የፈተናው ወረቀቶች እስኪሰበሰቡና እንድትወጡ እስኪፈቀድ መጠበቅ አለባችሁ።

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም!**

አካባቢ ሳይንስ ጥር 2018ዓ.ም

LIVEWORKSHEETS

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክ/ከተማ ትምህርት/ጽ/ቤት የአንደኛ መንፈቅ አመት የ6ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ሞዴል ፈተና

**የተሰጠው ሰዓት 1- ሰዓት**

**የጥያቄዉ ብዛት 40**

**ትዕዛዝ፡-ለእየአንዳንዱ ጥያቄዎች ከቀረቡት አራት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘዉን ፊደል በመምረጥ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁር(ሪ)፡፡**

1. ከሚከተሉት ሀገራት ዉሰጥ ኢትዮጵያን በስተ ሰሜን አቅጣጫ የሚያዋስናት ሀገር የቱ ነዉ?
   ሀ.ኬንያ ሐ. ሶማሊያ
   ለ.ኤርትራ መ. ሱዳን
2. ከሚከተሉት ሀገራት ዉስጥ የኢትዮጵያ አጎራባች ሀገር ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ጅቡቲ ሐ. ግብፅ
   ለ. ሶማሊያ መ. ኬንያ
3. የአክሱም ሀዉልት ፍጹማዊ መገኛን የሚያመላክተዉ የቱ ነዉ
   ሀ. $8^0$ 25' 58" ሰሜን ኬክሮስ እና $35^0$ 36' 35" ምስራቅ ኬንትሮስ
   ለ. $4^0$ 7' 47"ሰሜን ኬክሮስ እና $38^0$ 43' 60" ምስራቅ ኬንትሮስ
   ሐ. $18^0$ 25' 58" ሰሜን ኬክሮስ እና $28^0$ 46' 25" ምስራቅ ኬንትሮስ
   መ. $12^0$ 22' 35" ሰሜን ኬክሮስ እና $33^0$ 45' 7" ምስራቅ ኬንትሮስ
4. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ ንድፈ ካርታን ለመስራት የሚያስችለን የቱ ነዉ?
   ሀ. ካርታዎቻቸዉ የሚዘጋጁ ቦታዎችን አለመለያት
   ለ. የቦታዎችን መነሻ አለማስቀመጥ
   ሐ. የቦታዎችን ንድፈ ካርታ በሀሳብ አለማስቀመጥ
   መ.የሚሳለዉን ካርታ ድንበር መወሰን
5. ከሚከተሉት ዉስጥ የጂፒኤስ ጥቅም ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ከሳትላይቶች ምስሎችን ለመዉሰድ
   ለ. የሰዎችን እንቅስቃሴ ለማወቅ
   ሐ. ካርታዎችን ለማዘጋጀት የሉበትን ቦታ ለማወቅ
   መ. ተጓዦች በአየር በባህር እና በመሬት ያሉበትን ቦታ ለማወቅ
6. ከሚከተሉት ምግብ መተላለፊያ ቱቦዎች ዉስጥ ምግብ የማይፈጭበት የቱ ነዉ?
   ሀ. አፍ ሐ. ጉሮሮ
   ለ. ጨጓራ መ. ትንሹ አንጀት
7. ከሚከተሉት ዉስጥ ቁስ አካል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ድንጋይ ሐ. ስኳር
   ለ. እንጨት መ. ብርሃን
8. ከአንድ አይነት አቶም ብቻ የተሰራ ቋሚ ስሪት ያላቸዉ ንጹህ ልዩ ቁሶች ምን ይባላሉ?
   ሀ. ንጥረ ነገሮች ሐ. ኦክሳይዶች
   ለ. ዉህዶች መ. ድብልቆች
9. ከሚከተሉት ዉህዶች ዉስጥ ኦክሳይድ የሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ካርቦን ዳይኦክሳይድ ሐ. ሶዲየም ክሎራይድ
   ለ. ሰልፈሪክ አሲድ መ. ካልሲየም ሃይድሮኦክሳይድ
10. ከአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ እስከ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ያለዉ ርቀት 3 ኪሎ ሜትር ቢሆን ይህ ርቀት በሜትር ስንት ዩሆናል?
    ሀ. 300ሜ ሐ. 3000ሜ
    ለ. 30000ሜ መ. 30ሜ

LIVEWORKSHEETS

11.እፅዋቶች የራሳቸዉን ምግብ የሚያዘጋጁበት የጉልበት ምንጭ የቱ ነዉ?

ሀ. የንፋስ ጉልበት ሐ. የፀሀይ ጉልበት

ለ. የነዳጅ ጉልበት መ. የእንጨት ጉልበት

12.ድምፅ በከፍተኛ ፍጥነት የሚተላለፍበት የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ጠጣር ሐ. ጋዝ

ለ.ፈሳሽ መ. ወና

13.ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ የአየር ንብረት ይዘት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ሙቀት ሐ.ንፋስ

ለ. ዝናብ መ. ከፍታ

14.ከሚከተሉት ዉስጥ የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ክልል ዉስጥ በጣም ሞቃታማ እና ደረቃማ የአየር ንብረት ክልል የቱ ነዉ?

ሀ. ዉርጫማ ሐ. ደጋማ

ለ. በረሃማ መ.ወይና ደጋማ

15.በአንድ ቦታ የፀሐይ ጨረር በቀጥታ የሚያርፍ ከሆነ ጨረሩ የሚያርፍበት የሙቀት መጠን ምን ይሆናል?

ሀ. ዝቅተኛ ሐ. በጣም ዝቅተኛ

ለ. መካከለኛ መ. ከፍተኛ

16.ከሚከተሉት ዉስጥ የተፈጥሮ ሀብት የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ.ቤት ሐ.አየር

ለ.መኪና መ.ወንበር

17.የአንታርክቲክ ክበብ በካርታ ወይም በሉል ላይ በየትኛዉ ንፍቀ ክበብ ላይ ይገኛል?

ሀ.ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ሐ.ምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ

ለ.ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ መ.ምስራቃዊ ንፍቀ ክበብ

18.ከሚከተሉት የዉሀማ ክፍሎች ዉስጥ ምስራቅ አፍሪካን የማያዋስነዉ የቱ ነዉ?

ሀ.ቀይ ባህር ሐ.ሜዲትራንያን ባህር

ለ.ኤደን ባህረ ሰላጤ መ.ህንድ ዉቅያኖስ

19.ከሚከተሉት ሀገራት ዉስጥ የአፍሪካ ቀንድ ሀገር የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ.ኤርትራ ሐ.ሩዋንዳ

ለ.ዩጋንዳ መ.ታንዛንያ

20.ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል የባህር በር የሌለዉ የቱ ነዉ?

ሀ.ኤርትራ ሐ.ሶማሊያ

ለ.ኬንያ መ.ኢትዮጵያ

21.ኦክስጅንና አልሚ ምግቦችን ለሰዉነታችን ህዋስ የሚሰራጩበት፣ካርቦንዳይ ኦክሳይድና ሌሎች ቆሻሻዎች በደም አማካኝነት የሚሔዱበት ሒደት ምን ይባላል?

ሀ.ደም ሐ.የደም ዑደት

ለ.ትንፈሳ መ.ስርአተ ልመት

22.ከሚከተሉት የደም ህዋሶች ዉስጥ ኦክስጅንን ከሳንባ ተቀብሎ በመሸከም ለመላ የሰዉነታችን ህዋሳት የሚያደርሰዉ የቱ ነዉ?

ሀ.ፕላትሌት ሐ.ነጭ የደም ህዋስ

ለ.ቀይ የደም ህዋስ መ.ፕላዝማ

LIVEWORKSHEETS

23.ከሳንባ በኦክስጅን የበለፀገ ደም በፑልሞናሪ ቬይን ተቀብሎ ወደግራ አቀባይ ልበ ገንዳ የሚልከዉ የልብ ክፍል የቱ ነዉ?

ሀ.ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ  ሐ.ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

ለ.ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ  መ.ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ

24.የልብ ምትን የምናዳምጥበት መሳሪያ ምን ይባላል?

ሀ.ስቴቶስኮፕ  ሐ.ቴሌስኮፕ

ለ.ማይክሮስኮፕ  መ.ሊቶስኮፕ

25.ከሚከተሉ ዉስጥ በጉርምስና እና በኮረዳነት ወቅት በወንዶች እና በልጃገረዶች ላይ የሚከሰተዉ ተፈጥሮአዊ ክስተት የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ.የድምፅ መጎርነን  ሐ.የጡንቻ መዳበር

ለ.የዳሌ መስፋት  መ.የክብደትና ቁመት መጨመር

26.ከሚከተሉት የመተንፈሻ አካላት ዉስጥ ለኦክስጅንና ለካርቦንዳይ አክሳይድ ወደ ደም ዉስጥ መግቢያና መዉጫ ሆኖ የሚያገለግለዉ የቱ ነዉ?

ሀ.አፍ  ሐ.ድህረአፍ

ለ.ትንክረት  መ.ሰርን

27.በድብልቅ ዉስጥ የሚገኝ ፈሳሽ ምንዝርን በዝግታ በማንቆርቆር ወይም በመቅዳት ከሌላኛዉ ካልሚሚዉ ጠጣር ወይም ፈሳሾች የምንለይበት ዘዴ ምን ይባላል?

ሀ.ትነት  ሐ.ጥልያ

ለ.ንጥረት  መ.ቀረራ

28.ከሚከተሉት ድብልቆች ዉስጥ የዋህድ ዘር የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. የአልኮልና የዉሃ ድብልቅ  ሐ.ወተት

ለ. ደም  መ. የአሸዋና የዉሃ ድብልቅ

29.ከሚከተሉት ዉስጥ ታዳሽ የጉልበት ምንጭ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. የፀሐይ ብርሃን  ሐ. የድንጋይ ከሰል

ለ. ነፋስ  መ. ዉሃ

30.አናጺዎች ቤት ሲያፈርሱ ሚስማርን ከእንጨት ላይ በመዶሻ ለመንቀል የሚጠቀሙበት የቀላል መኪና አይነት የቱ ነዉ

ሀ. ዘንባይ ወለል  ሐ. ሽክርክሪት

ለ. ሽብልቅ  መ. መፈንቅል

31.ነገሮችን ለመስቀልና ከጉድጓድ ዉሃ ለማዉጣት የምንጠቀምበት ቀላል መኪና የቱ ነዉ?

ሀ. መፍቻ  ሐ. ሽብልቅ

ለ. ሽክርክሪትና ዘንግ  መ. መፈንቅል

32.ከሚከተሉት ዉስጥ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. የሙቀት መጠን  ሐ. ከባህር ያለዉ ርቀት

ለ. የዝናብ መጠን  መ. የአየር ግፊት

33.በደቂቃ በሰዓታት በቀናት እና በየወቅቱ የተወሰነ ቦታየሚታየዉ የአየር ለዉጥ ምን ይባላል?

ሀ. የአየር ሁኔታ  ሐ. ኬክሮስ

ለ. የአየር ንብረት  መ. ከፍታ

34.የምስራቅ አፍሪካ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኙ አከባቢዎች ዝናብ ሚያገኙት

ሀ. ከሰኔ እስከ መስከረም  ሐ. ከጥቅምት  እስከ ታህሳስ

ለ. ከታህሳስ እስከ የካቲት  መ. ከመስከረም እስከ ህዳር

LIVEWORKSHEETS

35.አመታዊ አማከኝ የዝናብ መጠናቸዉ ከ250 ሚ.ሜ በታች የሆኑ ቦታዎች ምን ተብለዉ ይጠራሉ?

ሀ. ደጋ ሐ.ወይናደጋ

ለ.በረሃ መ.ዉርጭ

36.ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ዉስጥ የትኛዉ በብረትና በወርቅ ማዕድናት ይታወቃል?

ሀ. ሶማሊያ ሐ. ኢትዮጵያ

ለ. ዩጋንዳ መ. ሞዛምቢክ

37.ከሚከተሉት ዉስጥ ዉጤታማ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ዘዴ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ስለተፈጥሮ ሀብት አያያዝ የወጡ ህግና ደንቦችን አለመተግበር

ለ. ባዮጋዝ መጠቀም

ሐ. በወንዞች አካባቢ ዕፅዋትን መትከል

መ. ዉሃን በአግባቡ መጠቀም

38.ቨርቲሶል የሚባለዉ የአፈር አይነት የሚገኛዉ የምስራቅ አፍሪካ ሀገር የት ነዉ?

ሀ. ታንዛንያ ሐ.ቡሩንዲ

ለ. ኤርትራ መ. ኢትዮጵያ

39.ደን ባልነበረበት ዛፎችን ማብቀል እንዲሁም ዕፅዋት ባልነበረበት ስፍራ ችግኞችን የመትካል ተግባር ምን ይባላል?

ሀ. ድነና ሐ. የእርከን ስራ

ለ. ዳግም ድነና መ. ዘር ማፈራረቅ

40.የምስራቅ አፍሪካ የማዕድን አጠቃቀም ተግዳሮት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. በሙያዉ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል እጥረት

ለ. አነስተኛ የሀገር ዉስጥ ፍላጎት መኖር

ሐ. በቂ መሰረተ ልማት መኖር

መ. የማዕድን ቁፋሮ ቴክኖሎጂ እጥረት

LIVEWORKSHEETS